ቁጥር፡ አ1162/11/15358

ጥቅምት 23 2017

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ለሶማሌ ፌደራሊስት ፓርቲ**

**ጅግጅጋ**

የሶማሌ ፌዴራሊስት ፓርቲ ሁለተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉበኤውን መስከረም 04 እና 05 2017 ዓ/ም አካሄዶ ሪፖርት ቀርቧል።የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ታህሳስ 21 ቀን 2017 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ፓርቲው ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ፤ የታዘቢዎችን ሪፖርትና የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ከአዋጅ ቁጥር 1162/11 አንፃር መርምሮታል።

ፓርቲው በጠቅላላ ጉባኤው አሻሽሎ ባቀረበው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 16.2 የፓርቲው ፕሬዝዳንት ምርጫ፤ አንቀፅ 17(1) ላይ የፓርቲው ምክትል ፕሬዝዳንትና በአንቀፅ 18(1) ላይ የፓርቲው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ዋና ፀሃፊ ምርጫን በተመለከተ ምርጫው ግልፅ፤ ፍትሐዊና ነፃ በሆነ መልኩ የሚደረግ መሆኑን የተገለፀ ቢሆንም ምርጫው በሚስጥር መሆን ያለበት መሆኑን አልተደነገገም።

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 74/3/ መሰረት ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፓርቲውን አመራሮች እና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልፅ፣ ነፃና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መንገድ የሚመረጡ መሆናቸውን ተደንግጓል።

በመሆኑም ከላይ በተዘረዘሩት የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፆች ላይ ፓርቲው በሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤው ማስተካከያ እስኪያደርግ የፓርቲው መተዳዳሪያ ደንብ አንቀፆች ታግደው የአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንቀፅ 74(3) ተፈፃሚነት እንዲኖረው በማለት ፓርቲው ያደረገውን ጠቅላላ ጉባኤ ቦርዱ ተቀብሎ ያፀደቀው መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
የፖለቲካ ፓርቲዎች

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገን
ሪስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-elec
of-ethiopi

ትዊተር
@NEBE

ኢሜል
contact@n

ድረ-ገጽ
www.ne

Scanned with CamScanner